DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Food & Nutrition Services

| | |
|---|---|
| ለ፡ | DCPS ቤተሰቦች |
| ከ፡ | ራብ ጃባር፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የምግብ እና ተመጣጣኝ ምግብ አገልግሎቶች |
| ቀን፡ | ነሐሴ 18 ቀን 2012 ዓ.ም (August 24, 2020) |
| ጉዳዩ፡ | የልጅ ተመጣጣኝ ምግብ ፕሮግራሞች፣ የምግብ ክፍያ ፖሊሲ፣ እና የአመጋገብ አቅርቦት እንክብካቤ |

## የUSDA የልጅ ተመጣጣኝ ምግብ ፕሮግራሞች

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ የተማሪን መማር እና ስኬታማነት ለማገዝ፣ ገንቢ ምግቦችን ማቅረብ በመቻሉ ኩራት ይሰማዋል። DCPS ከአሜሪካ የግብርና መምሪያ (United States Department of Agriculture (USDA) ጋር በመተባበር፣ የልጅ ተመጣጣኝ ምግብ ፕሮግራሞችን እና በዲሲ የጤናማ ትምህርት ቤቶች ድንጋጌ (DC Healthy Schools Act) የተቀረጸውን መመሪያዎችን ተከትሎ ይሠራል። በUSDA የትምህርት ቤት የጠዋት ቁርስ ፕሮግራም፣ በብሄራዊ የትምህርት ቤት ምሣ ፕሮግራም፣ የልጅና አዋቂ እንክብካቤ የምግብ ፕሮግራም፣ ለጋ (fresh) የሆኑ ፍራፍሬዎችና አታክልቶች ፕሮግራም፣ እና የበጋ (Summer) የምግብ አገልግሎት ፕሮግራም፤ ላይ ትምህርት ቤቶቻችን ይሣተፋሉ።

## የትምህርት ቤት ምግብ አገልግሎት፣ በኮሮና ቫይረስ የሕዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ወቅት

ለትምህርት ዓመት 2020-2021፣ በCovid-19 የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ምክንያት፣ በምናባዊ (virtual) እና/ወይም ድቅል (hybrid) የመማር ሞዴል እንዲሠጥ ተደርጎ በሚካሄድበት ወቅት፣ ለDCPS ተማሪዎች፣ በተመረጡ የትምህርት ቤት ቦታዎች ቁርስ እና ምሣን ለመውሰድ (pick up) ዝግጁ እንዲሆኑ አድርጎ፣ አገልግሎት ይሠጣል። ለአንድ ተማሪ፤ አንድ ቁርስ እና አንድ ምሣ፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን ይሰጣል። ወላጆች ወይም እንክብካቤ ሰጪዎች፣ የDCPS ተማሪ(ዎችን) ወክለው ምግቦችን መውሰድ (pick up ማድረግ) ይችላሉ። በቦታው ተገኝተው ለመውሰድ (pick up) ሲመጡ፤ የተማሪ ስም፣ የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር (ID)፣ እና የትምህርት ቤቱ ስም፤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። አሁን በቅርቡ ተስተካክሎ የተዘጋጀ የትምህርት ቤት ምግብ ማግኛ ቦታዎች ዝርዝርን እና ተጨማሪ መረጃን ማግኘት ከፈለጋችሁ፤ እባካችሁን፣ https://dcps.dc.gov/food ጎብኙ። በCovid-19 የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ወቅት፣ በምናባዊ (virtual) እና/ወይም ድቅል (hybrid) የትምህርት ቤት መማር ወቅት፤ ሁሉም ምግቦች ለDCPS ተማሪዎች በነፃ የሚሰጡ ይሆናል።

## የምግብ ዋጋዎች እና ነፃና ቅናሽ ዋጋ ያላቸው ምግቦች

ሙሉ ለሙሉ በአካል ተገኝቶ መማር (in-person) ሲጀመር፣ የሚከተሉት የምግብ ዋጋዎች በስራ ላይ ይውላሉ፡ ቁርስ (Breakfast)፡ በነፃ ሲሆን፤ ምሣ ደግሞ፡ $3.00 ይሆናል። ለእርስዎ ትምህርት ቤት በተለየ ሁኔታ ስላለው የምግብ ፕሮግራሞች ለማወቅ፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎን ያነጋግሩ።

ተማሪዎ ከሚከተሉት በአንደኛው መንገድ አማካኝነት፣ ለነፃ ምሣ ብቁ ሊሆን/ልትሆን ይችላሉ፡

1. ተማሪዎች ከ86ቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንዱ፣ በማህበረሰብ ብቁነት ዝግጅት ፕሮግራም (Community Eligibility Provision Program (CEP) ተሳታፊ ከሆኑ፣ የትምህርት ቤት ዝርዝሮቹን ለመመልከት፤ እባክዎን ከዚህ በታይ ያለውን ድህረ ገጽ ይጎብኙ ወይም ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ፡

   https://dcps.dc.gov/page/community-eligibility-provision-cep-schools.
2. በቀሪዎቹ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ የDCPS ተማሪዎች ነፃ ምግቦችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ የሚችሉት፡
   a. በቤተሰባቸው ውስጥ፣ ከ'ተጨማሪ ተመጣጣኝ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP)'፣ ከ'Food Distribution Program on Indian Reservations (FDPIR)'፣ ወይም ከ'ጊዜያዊ የችግረኛ ቤተሰቦች ድጋፍ (Temporary Assistance for Needy Families (TANF)'፣ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚቀበሉ ተማሪዎች።

b. ተማሪዎች፣ ማደጎ (foster) ልጆች የሚባሉት፤ በሕጋዊ የማደጎ (foster) እንክብካቤ ሰጪ ድርጅት ወይም ፍርድ ቤት ኃላፊነት ስር ያሉ ወይም ደግሞ እንደ፤ ቤት አልባ፣ ስደተኛ፣ በምድቡ ብቁ የሆኑ ወይም ከመኖሪያቸው የጠፉ (runaway) ናቸው።

c. ነፃ እና ቅናሽ ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (FARM) ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉት፣ በፌደራል የገቢ ብቁነት መመሪያዎች ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ ነው።

ሁሉም በገቢያቸው ብቁ የሆነ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ፣ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ልጆች፤ የኢሚግሬሽን ሁኔታቸም ምንም ሆነ ምን የምግብ ጥቅማ ጥቅሞችን ያገኛሉ። *ተማሪዎ ለነፃ ምግቦች ብቁ ከሆነ፣ እባክዎን የ2020 - 2021 ነፃ እና ቅናሽ ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Reduced-Price Meal (FARM) ማመልከቻ በኦንላይን ላይ በ* https://www.myschoolapps.com/Application እባክዎን አጠናቀው ይሙሉ።

**ማስታወሻ:** በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት፣ አዲስ ቅጽ ተሞልቶ መጠናቀቅ አለበት። ተጨማሪ መረጃዎች እዚህ ይገኛሉ: https://dcps.dc.gov/publication/free-and-reduced-priced-meals-farm-application.

| **የፌደራል የገቢ ብቁነት መመሪያዎች፤ ለSY 2020-2021** | | | |
|---|---|---|---|
| **የቤተሰብ መጠን** | **ዓመታዊ ገቢ** | **ወርሃዊ ገቢ** | **ሣምንታዊ ገቢ** |
| 1 | $23,606 | $1,968 | $454 |
| 2 | $31,894 | $2,658 | $614 |
| 3 | $40,182 | $3,349 | $773 |
| 4 | $48,470 | $4,040 | $933 |
| 5 | $56,758 | $4,730 | $1,092 |
| 6 | $65,046 | $5,421 | $1,251 |
| 7 | $73,334 | $6,112 | $1,411 |
| 8 | $81,622 | $6,802 | $1,570 |
| **ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ግለሰብ** | $8,288 | $691 | $160 |

## የአካባቢ (Local) የምግብ ሂሣብ ክፍያ ፖሊሲ

የምግብ የሂሣብ ክፍያ ፖሊሲያችንን አጠቃላይ ዝርዝሮች ለማግኘት፣ እዚህ ይጎብኙ: https://dcps.dc.gov/page/meal-prices-and-payment

<u>የምግብ ሂሣብ ክፍያዎች</u>

የምሣ ምግቦች ክፍያዎችን ከሚከተሉት በአንደኛው መንገድ ያስገቡ:

1. የክሬዲት/ዴቢት (credit/debit) ካርድን በመጠቀም በmyschoolbucks.com ላይ የኦንላይን የክፍያ አገልግሎትን በመጠቀም መክፈል፤ (የአገልግሎት ክፍያ የሆነው $2.49፣ በእያንዳንዱ ግብይት (transaction) ያስጨምራል)፤ ወይም

2. ቼክ ወይም መኒ ኦርደር (money order) በመላክ፤ (የተማሪ የመታወቂያ ቁጥር (ID#) በቼኩ/መኒ ኦርደሩ ላይ መፃፍ አለበት)፤ ክፍያው የሚላከው ለማን እንደሆነ በሚጠይቀው ቦታ ላይ፤ **ለ:** 'DC Treasurer' በመፃፍ ካስገቡ በኋላ ወደሚከተለው አድራሻ ይላኩት:

DCPS Food and Nutrition Services
1200 First Street NE, 9th Floor
Washington, DC 20002

በተማሪው አካውንት ውስጥ ምንም ገንዘብ ባለመኖሩ ምክንያት፣ ተማሪዎች ምግብ ማግኘት በፍጹም አይከለከሉም ወይም ሌላ አማራጭ የሆነ የምግብ ዓይነት እንዲሰጣቸው አይደረግም። የተመገቡት ምግብ ወዲያውኑ ወደ ተማሪዎ አካውንት ውስጥ ተቀናሽ እንዲሆን ያደርገውና፣ የምግብ አጠቃላይ ገንዘቡን ከዜሮ በታች (negative balance) እንዲኖረው ያደርገዋል። ከዜሮ በታች (negative balance) የምግብ ገንዘብ ያለባቸው ተማሪዎች፣ ከዜሮ በታች አካውንት እንዳላቸው ለሌሎች የሚያሳይበት መንገድ አይኖረውም፤ ለሁሉም ተማሪዎች አንድ ዓይነት የሆነ የምግብ ምርጫዎችን ያገኛሉ።

<u>የምግብ አጠቃላይ የገንዘብ ድምር ከዜሮ በታች ሲያንስ</u>

ትህትና በተሞላው ሁኔታ እንደገና ለማስታወስ ያህል፣ አንድ ጊዜ የተማሪው ጠቅላላ ሂሳብ $9.00ን ካለፈ፣ (3 የምሣ ክፍያዎች ሲቀሩት)፣ ወደመኖሪያ ቤታቸው የማስታወሻ መገናኛዎች (የስልክ ጥሪ፣ ቴክስት (text)፣ ኢሜል) በማሽን የተቀዳ (automated ) መልዕክት አማካኝነት ማስታወሻ ይደርሳችኋል። በማሽን የተቀዳ (automated ) መገናኛ መልዕክቶቹ፣ ከዜሮ በታች የሆነ ሂሳብ (negative) የምግብ ሂሳብ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ እየተደጋገመ ይላካል። ቀደም ሲል የተጠቀሰው የክፍያ መንገዶች፤ እንደ (በኦንላይን እና በቼክ/መኒ ኦርደር/money order) ከዜሮ በታች ያለውን የምግብ አጠቃላይ ሂሳብ ለመክፈል መጠቀም ይቻላል።

ተማሪው ምሣ መመገቡን እስከቀጠለ ድረስ፣ የምግብ አጠቃላይ ሂሳቡም እየጨመረ ይሄዳል። የምግብ አጠቃላይ ሂሳቡን መቆጣጠር የሚችሉት፣ ለልጅዎ የምግብ አካውንት ውስጥ ገንዘቡን በመሙላት ይሆናል። ማንኛውም ለምግብ ያልተከፈለ አጠቃላይ ሂሳብ፣ እስካልተከፈለ ድረስ፤ ወደሚቀጥለው የትምህርት ዓመት፣ ያልተከፈለው ሂሳብ ይተላለፋል። ማንኛውንም ክፍያ ሲያደርጉ፣ መጀመሪያ ሳይከፈል ከዜሮ በታች የሆነውን ሂሳብ ተቀናሽ በማድረግ ይጀምራል። የተማሪው የምግብ አጠቃላይ ሂሳቦች ከዜሮ በታች መሆን፣ ተማሪውን ከምርቃት እንደማያዘገየው፣ እባክዎን ያስታውሱ። የDCPS የምግብና የተመጣጣኝ ምግብ አገልግሎቶች፣ ስለ ከዜሮ በታች የምግብ ሂሣቦች እና መልሶ መክፈልን በተመለከተ ለሚጠየቁ ጥይቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚቻለውን ጥረት ያደርጋል።

በማሽን የተቀዳ (automated ) መገናኛዎች፤ የFARM ማመልከቻዎቻቸውን በማጠናቀቅ ሁሉም ተማሪዎች ለነፃ ምግቦች ብቁነታቸውን ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባውን ማመልከቻን ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ፤ እንዲሁም ለቤተሰቦች ለማስታወስም ጥቅም ላይ ይውላል።

ይህ ተቋም ለሁሉም፣ በዕኩልነት ዕድል ሰጪ ነው። የዚህን ደብዳቤ የተተረጎመው ስሪት ለማየት፣ እባክዎን https://dcps.dc.gov/page/meal-prices-and-payment ይጎብኙ።

## የአመጋገብ (Dietary) እንክብካቤ መጠየቂያ ቅጾች

ከUSDA የልጅ ተመጣጣኝ ምግብ ፕሮግራም (Child Nutrition Program) በሚቀርቡ ምግቦች ላይ፤ ከምግብ በሚመጣ አለርጂ (allergy)፣ በሕክምና ሁኔታ፣ ወይም በፍልስፍና/በሃይማኖት ምክንያቶች፤ ተማሪዎ ልዩ የሆነ የአመጋገብ/የምግብ ዕቅድን ካስፈለጋችሁ፣ ልታሳውቁን ይገባል። እባክዎን የአመጋገብ (dietary) እንክብካቤ መጠየቂያ ቅጽን በ(https://dcps.dc.gov/node/1415741) ሞልተው ያጠናቁ እና ተሞልቶ የተጠናቀቀውን ቅጽ ለትምህርት ቤትዎ ነርስ (nurse) ወይም በምናባዊ (virtual) እና/ወይም ድቅል (hybrid) መማር ወቅት፤ ሌላ ክፍት ሆኖ ምግብን የሚያቀርብ ቦታ ውስጥ፣ ያስገቡ። እባክዎን፣ ይህን የምግብ ዝርዝሮች (menus) ሂደት ማከናወኛ እና ማስፋፊያ ሊሆን የሚችለውን በቂ ጊዜ ይስጡት። FNS፣ ከተገቢው እንክብካቤ አቅም በላይ የሆነን ጥያቄዎችን የመከልከል መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

ማንኛውም ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ የምግብ እና ተመጣጣኝ ምግብ አገልግሎቶችን በ202-299-2159 ወይም በኢሜል በfood.dcps@k12.dc.gov እባክዎን ያነጋግሩ።

ከሰላምታ ጋር፣

ራበርት M. ጃባር
ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የምግብ እና ተመጣጣኝ ምግብ አገልግሎቶች